# የዋዜማ ጠብታ፡ በኦሮሚያው ተቃውሞ የደረሰውን ስብዓዊ ጉዳት የሚመለከት ሪፖርት ይፋ ሆነ

By wazemaradio

MAR 14, 2016

- *“የኦሮሚያ ክልል በ18 ዞኖች እና በ342 ወረዳዎች የተከፋፈለ ሲሆን ሰመጉ በ33 ወረዳዎች ብቻ ባደረገው የመስክ ምርመራ ባገኘው ውጤት መሰረት 103 ሰዎች የተገደሉ ሲሆን 57 ሰዎች በጥይት የመቁሰል እና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል”*



*Young Oromo Protestors SM*

(ዋዜማ)-የቀድሞው ኢሰመጉ ያሁኑ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) በሀገሪቱ በተከሰቱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ዙሪያ በየጊዜው የሚያወጣቸው ልዩ ሪፖርቶች በጉዳዩ ዙሪያ በሚሰሩ ተቋማት ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታ የሚሰጣቸው ናቸው

የአሜሪካ መንግስት በስቴት ዲፓርትመንት በኩል በየዓመቱ ለንባብ የሚያበቃቸው ጠንካራ እና ተቺ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ሪፖርቶች የሚመረኮዙት የሰመጉን መግለጫዎች ነው በሚል በመንግስት ዘንድ ጥርስ ከተነከሰበት ቆየ፡፡ ሰመጉ ከተመሰረተበት ከ1984 ጀምሮ አንድ ሁለት እያለ ሪፖርት ማውጣት ከጀመረ 140ኛው ላይ ደርሷል፡፡ ዛሬ መጋቢት 5 በፅህፈት ቤቱ በተሰበሰቡ ዲፕሎማቶች እና ጋዜጠኞች ፊት የተሰራጨው ልዩ ሪፖርት ሙሉ ትኩረቱንያደረገው ከህዳር ወር 2008 ዓ ም ጀምሮ የአዲስ አበባና የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላንንበመቃወም በተለያዩ አካባቢዎች እየተደረጉ ባሉ ሰላማዊ ሰልፎች እና እየተወሰዱ ባሉ እርምጃዎች ላይ ነው፡፡

በሰላሳ አራት ገፅ የተዘጋጀው ሪፖርት በተለያዩ አካባቢዎች የደረሰውን የሰው እና የንብረት ጉዳት እና የምርመራ
ስራው እንዴት እንደተከናወኑ የሚያሳዩ ዝርዝሮችን በፎቶግራፍ ጭምር አስደግፎ የያዘ ነው፡፡ “የመንግስት የጸጥታ ኃይሎች ለተቃውሞ በወጡ ዜጎች ላይ በወሰዷቸው ከመጠን ያለፉ የኃይል እርምጃዎች የበርካታዜጎች ሕይወት ጠፍቷል” ይላል ሪፖርቱ በመግቢያው፡፡ “በርካታ ሰዎች በጥይት ተመትተው የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ በርካታ ሰዎች ታስረዋል፣ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ሰዎች የደረሱበት አይታወቅም፣ ከፍተኛ ኪሳራ ያስከተለ ከባድ የንብረት ውድመት ደርሷል፡፡”

በኦሮሚያ የተቀሰቀሰው ተቃውሞ ሰፊ አካባቢን ቢያካልልም ሰመጉ ባለው ውሱን አቅም ምክንያት ባለሙያዎቹን በመላክ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ምርመራ ማከናወን የቻለው ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል በተባሉ አካባቢዎች ብቻ ነው፡፡ የኦሮሚያ ክልል በ18 ዞኖች እና በ342 ወረዳዎች የተከፋፈለ ሲሆን ሰመጉ በ33 ወረዳዎች ብቻ ባደረገው የመስክ ምርመራ ባገኘው ውጤት መሰረት 103 ሰዎች የተገደሉ ሲሆን 57 ሰዎች በጥይት የመቁሰል እና ከባድ

CATEGORIES

About Wazema
Art and Culture
Benegerachin Lay-Discussion
Book Review
Current Affairs
Fake News alert
Home
Letter From Addis
News
PODCASTS
Talking points
Uncategorized
Video
Wazema Dossier
Wazema Forum

WAZEMA MEDIA

Wazema Media is legally registered organization founded in 2014 by Ethiopian exiled journalists, currently based in Addis Ababa, Ethiopia.

የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። በ22 ሰዎች ላይ ማሰቃየት እና ድብደባ መፈፀሙን፣ 84 ሰዎች መታሰራቸውን እንዲሁም 12 ሰዎች የደረሱበት ወይም ያሉበት አለመታወቁን ሪፖርቱ በዝርዝር ያስቀምጣል።

ግድያዎቹም ሆኑ ሌሎቹ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች አንድ የምርመራ ዘገባ ሊያሟላቸው በሚገባቸው መሰረታዊ መረጃዎች ዳብረው ቀርበዋል። በሪፖርቱ የተገደሉ እና ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ስም፣ ዕድሜ፣ የመኖሪያ አድራሻ፣ ሁነቱ የተከሰተበት ቦታ እና ሰዓት እስከ ተቀበሩበት ቦታ ድረስ በተብራራ ሁኔታ ተቀምጠዋል። አብዛኞቹ ሟቾች ዕድሜያቸው ከ30 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች፣ ተማሪዎች እና አዳጊዎች ናቸው። የግድያ ፈፃሚዎቹን ማንነት በተመለከተ ከአንድ ሁለት ቦታ በስተቀር በጥቅሉ በታጠቁ የመንግስት የፀጥታ ኃይሎች፣ የመከላከያ ሰራዊት፣ የአጋአዚ ጦር አባላት፣ የፌደራል/ ኦሮሚያ ፖሊስ አባላት በማለት ብቻ ይገልፃቸዋል።

ሰመጉ በጽህፈት ቤቱ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ወቅት የገዳዩቹን ማንነት በሪፖርቱ ያለመግለጹ ጉዳይ ተነስቶ ነበር። የሰመጉ ምክትል ሊቀመንበር አቶ ቁምላቸው ዳኜ ለጥያቄው በሰጡት መልስ የድርጊቱን ፈፃሚዎች ቢያውቁም “ከዳኝነት በፊት እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር” መብታቸውን ለመጠበቅ ሲባል በሪፖርቱ አለመካተቱን አስረድተዋል። “እከሌ እከሌን ገድሏል ብለን ልናወጣ አንችልም” ይላሉ አቶ ቁምላቸው። “ለሚመለከተው ለሚመረምር አካል ለማቅረብ ግን ዝግጁ ነን” ሲሉ እንደ ሁልጊዜውም ከፍትህ አካላትም ሆነ ከሌሎች የመንግስት ተቋማት ጋር ለመተባበር ያላቸውን ፍላጎት ገልጸዋል።

አቶ ቁምላቸው ይህን ቢሉም ሰመጉ ያለው መረጃ ላይ ተመስርተው ሲያብራሩ ብዙዎቹ ግድያዎች የተፈፀሙት ከሰላማዊ ሰልፉ በኋላ መሆኑን፣ አንዳንዶቹ ግድያዎች የተፈፁሙት ከፖሊስ ጣቢያ ፊት እንደሆነ እና አንዳንዶቹ ሟቾች ከቤት ተወስደው እንደሆነ እና ፈጻሚዎቹም የመንግስት ሰዎች መሆናቸውን ሳይጠቁሙ አላለፉም። አንዳንዶቹ የድርጊቱ ፈጻሚዎች ከግድያው በኋላ ከአካባቢያቸው በክልሉ ውስጥ ወዳለ ሌላ ቦታ መዛወራቸውን አስረድተዋል።

የሰመጉ ሪፖርት በኦሮሚያ በተቀሰቀሰው ተቃውሞ ዙሪያ ለሚነሱ በርካታ ጥያቄዎች የተሟላም ባይሆን ውስን ምላሾችን ይሰጣል። በተቃውሞው ዙሪያ የታጣውን የገለልተኛ አካል ማጣራትም በፊር ቀዳጅነት ያከናወነ ነው። ከደረሰው ጉዳት ተሻግሮም መንስኤውን ለመፈተሽ የሞከረ ነው።

“መንግስት የተቀናጀ ማስተር ፕላኑን በማርቀቅ ሂደት ዜጎችን በተለይም በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ የኦሮሚያ
ገጠርና ከተማ ነዋሪዎችን ባለማሳተፉ፣ ረቂቅ ሰነዱንም እስከዛሬ ለህዝብ ይፋ ባለማድረጉ የብዙ ዜጎችን ሕይወት ለቀጠፈውና የአካልና የንብረት ጉዳት ላስከተለው ቀውስ ምክንያት ሆኗል” ይላል ሪፖርቱ ስለ ተቃውሞው መንስኤ ሲያብራራ። “ረቂቅ ማስተር ፕላኑ ለባለሙያዎችና ለሌሎችም ባለድርሻ አካላት ቀርቦ ግልፅ ውይይት፣ ክርክር እና ትችት ሊደረግበት ሲገባ ለዓመታት በምሥጢር መያዙና ይዘቱም ለዜጎች አለመገለፁ ለጥርጣሬ፣ ለውዥንብርና ደም ላፋሰሰ ግጭት መንስዔ ሆኗል።”

ሙሉ መግለጫውን እነሆ https://www.luminpdf.com/viewer/wi7239WPq8DwhMWsa

« የኢትዮጵያ መንግስት የገንዘብ ኖት በሀገር ውስጥ ለማተም እየተሰናዳ ነው

በኮንሶ በተቀሰቀሰ ግጭት ሰዎች ተገደሉ »

By wazemaradio

Tweets from @Wazemaradio

W..
· 8h

- ኢትዮጵያ የኬንያ ኩባንያዎች ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መዳረሻ በመኾን ከምሥራቅ አፍሪካ ቀዳሚውን ደረጃ ይዛለች ተባለ።

እና ሌሎች ዜናዎችን ያድመጡ።

👉🏾 youtu.be/LDa776ugSDI #Ethiopia

1 5

W..
· 22h

Replying to @Wazemaradio

ጨምረውም፣ የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት ተዋጊዎች ጥቃቶቱን መከተዋል ብለዋል። በመንግስት በኩል ስለጉዳዩ የተባለ ነገር የለም። በኦሮሞ ነጻነት